የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 50.
ADDIS ABABA 11th August, 2008


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ
…ገጽ ፬ሺ፩፻፷፰


CONTENTS


**Proclamation No. 591/2008**

The National Bank of Ethiopia Establishment (as Amended) Proclamation Page 4168


## አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት የተረጋጋ የዋጋ፣ የውጭ ምንዛሬ ምጣኔና ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተመጣጠነ ዕድገት ተስማሚ የሆኑ ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን ስለአለበት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "ሥልጣን የተሰጠው መንዛሪ" ማለት ከባንኮች በስተቀር በውጭ አገር ገንዘብ ግብይት ለመሠማራት ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፤

## PROCLAMATION NO. 591/2008.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE NATIONAL BANK OF ETHIOPIA ESTABLISHMENT PROCLAMATION

**WHEREAS**, for the rapid economic development of Ethiopia stable price and foreign exchange rate and healthy financial system are being necessary;

**WHEREAS**, it is necessary for the National Bank of Ethiopia to undertake such other activities as are conforming to the proportional economic growth of Ethiopia;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "the National Bank of Ethiopia Establishment (as Amended) Proclamation No. 591/2008".

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "authorized dealer" means any person other than a bank, which is authorized by the National Bank to engage in foreign exchange transactions;

፪/ "የባንክ ሥራ" ማለት የሚከተሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፤

ሀ) ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አለው ብሎ በፈቀደው የገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል፤

ለ) የባንክ ሥራ በሚሠራው ሰው ሂሣብና ኃላፊነት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) የተመለከተውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው ብድሮች፣ ኢንቨስትመንቶችና ሌሎች ጉዳዮች የማዋል፤

ሐ) በገንዘብ መልክ ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የመግዛትና የመሸጥ፤

መ) በራሳቸውም ሆነ በደንበኞቻቸው ስም ለሌሎች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች ገንዘብ የማስተላለፍ፤

ሠ) በገንዘብ ማስከፈያ፣ በሐዋላና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች በተረጋገጡ የዕዳ ሰነዶች በቅናሽ የማበደርና የማስተላለፍ፤

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሠ) በተመለከቱት ተግባራት የተሠማራ ባንክ እንዲሠራቸው በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያገኙ በተለምዶ እንደባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፤

፫/ "ባንኮች" ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠሩ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሠጣቸው ኩባንያዎች ወይም የመንግሥት ባንኮች ናቸው፤

፬/ ""የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የሚቋቋም ፈንድ ነው፤

፭/ ""የውጭ አገር ገንዘብ" ማለት ከኢትዮጵያ ገንዘብ በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጭ በማናቸውም ሃገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚ ደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ያሳወቀው ማናቸውም ገንዘብ ነው፤

፮/ "የውጭ ምንዛሪ" ማለት በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸው የውጭ ሃገር ገንዘቦችና በውጭ ሃገር ገንዘብ የተዘጋጁ የክፍያ ማዘዣ ቼኮች፣ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ ሰነዶች፣ ድራፍቶች፣ ሴኪዩሪቲዎች፣ እንደዚሁም ሌሎች የሚተላለፉ ሰነዶችና በውጭ ሃገር ገንዘብ የተያዙ የባንክ ሂሳቦች ወይም የሚከፈሉ ወይም በውጭ ሃገር ሂሣብ ወይም የማቻቻል አሠራር የሚደረግባቸው ንብረቶች ማለት ነው፤

2/ "banking business" means including the following:

a) receiving funds from the public as deposit through means that the National Bank has declared to be an authorized manner of receiving funds;

b) under the account and risk of the person undertaking banking business to use the funds referred to under paragraph (a) of this Sub-Article, in whole or in part, for loans, investments and for purposes that the National Bank has declared to be appropriate;

c) the buying and selling of gold and silver bullion and foreign exchange;

d) the transfer of funds to other domestic and foreign persons in the name of the banks themselves or their customers;

e) the discounting and negotiation of promissory notes, drafts, bills of exchange and other evidence of debt;

f) any other activity recognized as customary banking business, which a bank engaging in the activities described from paragraphs (a) to (f) of this sub-article is authorized to undertake by the National Bank;

3/ "banks" mean companies licensed by the National Bank to undertake banking business and banks owned by the Government;

4/ "deposit insurance fund" means a fund to be established in accordance with regulation to be issued by the Council of Ministers;

5/ "foreign currency" means any currency other than Ethiopian legal tender which is legal tender in any country outside Ethiopia as to which the National Bank has declared to be acceptable for payment in Ethiopia;

6/ "foreign exchange' means any foreign currency, cheques, bills of exchange, promissory notes, drafts, securities, and other negotiable instruments, expressed in foreign currency as well as bank balances in account held in foreign currency or assets in the form of foreign account crediting or set-off arrangements, expressed or payable in foreign currencies provided they are acceptable by the National Bank;

፯/ "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፤

፰/ "መድን ሰጪዎች" ማለት አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋሙ የመድን ኩባንያዎች ናቸው፤

፱/ "ገንዘብ-አከል ንብረት" ማለት ከገንዘብ ተቋማት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ) ጥሬ ገንዘብ፤

ለ) በብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባንኮች ያለ ተቀማጭ ገንዘብ፤

ሐ) በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸውና ያለገደብ ሊተላለፉ የሚችሉ በብር ወይም በውጭ ምንዛሪ ተከፋይ የሆኑ ንብረቶች፤

መ) በብሔራዊ ባንክ በየጊዜው ገንዘብ-አከል ተብለው ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች ንብረቶች፤

፲/ "ሌሎች የገንዘብ ተቋማት" ማለት አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግና ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት የተቋቋሙ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋሞች፣ የፖስታ ቁጠባ፣ የገንዘብ አስተላላፊዎችና ሌሎች መሠል ተቋማት ማለት ነው፤

፲፩/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የሀገሪቱ ማዕከላዊ ባንክ የሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፲፫/ "በውጭ ምንዛሪ የሚፈፀም ግብይት" ማለት

ሀ) የውጭ ምንዛሪ ማስተላለፍ፣ መበደር፣ ማበደር፣ ማዛወር፣ መመንዘር፣መግዛት፣ መሸጥ፣ መቀበል፣ መክፈል ወይም ሂሣብ ውስጥ ማስ ገባት፤ እና

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ የውጭ ምንዛሪ ማስተላለፍን፣ መበደርንና ማበደርን፣ ማዛወርን፣ መመንዘርን፣ መግዛ ትን፣ መሸጥን፣ መቀበልን፣ መክፈልን ወይም በሂሣብ ውስጥ ገቢ ማድረግን የሚያስከትል ውለታ፣ ስምምነት ወይም መግባባት ነው፤

፲፬/ "ዋጋ ያለው ዕቃ" ወይም "ዋጋ ያለው ነገር" ማለት ማናቸውም የገንዘብ ዋጋ ያለው ዕቃ ነው። ሆኖም በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ላይ የተመለከተ ውን የመንገደኛ ሻንጣና መንገደኛ ወደ ኢትዮጵያ ይዞት የሚመጣውን የውጭ ምንዛሪ አይጨምርም።

7/ "Government" means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

8/ "insurers" means insurance companies established in accordance with the appropriate law of Ethiopia;

9/ "liquid assets" mean in relation to financial institutions include:

a) cash;

b) deposits in the National Bank and other domestic and foreign banks acceptable by the National Bank;

c) assets readily convertible into cash expressed and payable in Birr or foreign currency acceptable by the National Bank;

d) such other assets as the National Bank may from time to time declare liquid assets;

10/ "other financial institutions" means micro-finance institutions, postal savings, money transfer institutions and other similar financial institutions established in accordance with the appropriate law of Ethiopia and as determined by the National Bank;

11/ "person" means any natural or juridical person;

12/ "National Bank" means the National Bank of Ethiopia, which is the central bank of the country;

13/ "transaction in foreign exchange" means:

a) the transfer, borrowing, lending, assignment, exchange, purchase, sale, receipt, payment or crediting of foreign exchange; and

b) the conclusion of any contract, agreement, arrangement or understanding, as a result of which any foreign exchange is transferred, borrowed, lent, assigned, exchanged, purchased, sold, received, paid or credited within or outside Ethiopia;

14/ "valuable good" or "valuable thing" means anything of value; but shall not include foreign exchange which a passenger brings with him into Ethiopia or any baggage of a passenger as provided in the Customs Tariff Regulation.

፲፭/ " ኩባንያ" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ህግ የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ አክሲዮኖቹ በሙሉ በኢትዮጵያዊያንና በኢትዮጵያዊያን ባለቤትነት በተቋቋሙ ድርጅቶች የተያዘ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተመዘገበና ዋና መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሆነ የአክስዮን ማህበር ነው።

## ክፍል ሁለት

## የብሔራዊ ባንክ አደረጃጀት፣ አመራርና ተግባራት

### ፫. ሕጋዊ አቋም

፩/ በትዕዛዝ ቁጥር ፴/፲፱፻፶፭ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ራሱን ችሎ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር ተቋም ሆኖ ይቀጥላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ኖሮት፣ በተለይም

ሀ) ውል የመዋዋል፣

ለ) የመክሰስና የመከሰስ፣ እና

ሐ) ንብረት የመያዝ፣ የማግኘት፣ ባለቤት የመሆንና ንብረቱን በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የማስወገድ፣

ችሎታ ይኖረዋል።

፫/ የብሔራዊ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል። ባንኩ፣

ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ማቋቋምና መዝጋት፣ እና

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ እና በውጭ አገር ወኪ ሎች እና አገናኝ ባንኮች መሰየምና መሻር፣

ይችላል።

፬/ የብሔራዊ ባንክ ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል።

፭/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ) የዳይሬክተሮች ቦርድ፣

ለ) በመንግሥት የሚሾሙ ገዥና ምክትል ገዥ፣ እና

ሐ) አስፈላጊ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል።

15/ "Company" means, as defined by the Commercial Code of Ethiopia, a share company in which the whole shares are owned by Ethiopian nationals and organizations established under the ownership of Ethiopian Nationals registered in accordance with the Ethiopian law and the head office is in Ethiopia.

## PART TWO

## ORGANIZATION, MANAGEMENT AND FUNCTIONS OFTHE NATIONAL BANK

### 3. Legal Status

1/ The National Bank of Ethiopia established by Order No. 30/1963 shall continue to exist as an autonomous institution and shall henceforth be governed by this Proclamation.

2/ The National Bank shall have its own juridical personality, and, in particular, the capacity to:

a) contract;

b) sue and be sued; and

c) acquire, own, possess and to dispose its property by sale or in any other manner.

3/ The National Bank shall have its head office in Addis Ababa and may:

a) establish and close branch offices in Ethiopia; and

b) designate, and revoke the designation of, agents and correspondents in Ethiopia and abroad.

4/ The National Bank shall be accountable to the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

5/ The National Bank shall have:

a) Board of Directors;

b) Governor and Vice Governor to be appointed by the Government; and

c) the necessary staff.

፮/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩታል። የብሔራዊ ባንክ ገዥ እና ምክትል ገዥ የቦርዱ ቋሚ አባላት ይሆናሉ። የቦርዱ ሊቀ መንበርና ቀሪዎቹ አራት አባላት በመንግሥት ይሾማሉ።

**፬. የብሔራዊ ባንክ ዓላማዎች**

የብሔራዊ ባንክ ዓላማ የተረጋጋ የዋጋና የውጭ ምንዛሪ ተመን ማስፈን፣ ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት መገንባትና ለኢትዮጵያ ፈጣን ኢኮኖሚ ልማት አመቺ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን ይሆናል።

**፭. የብሔራዊ ባንክ ሥልጣንና ተግባር**

ብሔራዊ ባንክ ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ ሕጋዊ ገንዘብን የመቅረጽ፣ የማተም ወይም የማስ ቀረጽ፣ የማሳተምና የማሠራጨት፤

፪/ በሕጋዊ መንገድ የወጡትን ሣንቲሞችና የገንዘብ ኖቶችን ማስወገድ ወይም እንዲወገዱ የማድረግ፤

፫/ የራሱን የዕዳና ክፍያ ሰነዶችን የማውጣት፤

፬/ የገንዘብና ብድር አቅርቦት በተፈለገው መጠን መገኘትን፣ እንዲሁም የወለድ ተመንና ሌሎች ክፍያዎችን የመወሰንና የመቆጣጠር፤

፭/ የውጭ ምንዛሪ ተመን ፖሊሲ የመቅረጽና ተግባራዊ የማድረግ፤

፮/ የኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሣቦች የማስተዳደርና የመምራት፤

፯/ ለባንኮች፣ ለመድን ሰጪዎችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ፈቃድ የመስጠትና ሥራቸውን የመቆጣጠር፤

፰/ የባንክ፣ የመድንና ሌሎች የገንዘብ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን የመፍጠር፤

፱/ ባንኮችና ፈቃድ የተሰጣቸው መንዛሪዎች ሊይዙት የሚችሉትን ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ገደብ የመወሰን፤

፲/ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የሚይዙትን የተጣራ የውጭ ምንዛሪ ልክ፣ እንዲሁም የውጭ ዕዳ ስምምነቶችና የዕዳውን ገደብ የመወሰን፤

፲፩/ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የአጭርና የረ ጅም ጊዜ የብድር አገልግሎት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲያገኙ የማድረግ፤

6/ The Board of Directors shall be composed of seven members. The Governor and the Vice Governor shall be permanent ex-officio members. The Chairperson of the Board of Directors and the remaining four members shall be appointed by the Government.

**4. Purpose of the National Bank**

The purpose of the National Bank is to maintain stable rate of price and exchange, to foster a healthy financial system and to undertake such other related activities as are conducive to rapid economic development of Ethiopia.

**5. Powers and Duties of the National Bank**

For the fulfillment of its purposes, the National Bank shall have the powers and duties to:

1/ coin, print or cause to be coined, printed and circulated the legal tender currency;

2/ dispose or cause to be disposed coins and notes issued legally;

3/ issue its own debt and payment instruments;

4/ regulate and determine the supply and availability of money and credit as well as the applicable interest rates and other charges;

5/ formulate and implement exchange rate policy;

6/ manage and administer the international reserves of Ethiopia;

7/ license and supervise banks, insurers and other financial institutions;

8/ create favorable conditions for the expansion of banking, insurance and other financial services;

9/ set limits on gold and silver bullion and foreign exchange assets which banks and authorized dealers can hold;

10/ set limits on the net foreign exchange position and on the terms and the amount of external indebtedness of banks and other financial institutions;

11/ make short term and long term refinancing facilities available to banks and other financial institutions as might be necessary;

፲፪/ ማናቸውም ዓይነት ተቀማጭ ገንዘብ ከውጭ አገር ምንጮች የመቀበል፤

፲፫/ ከማንኛውም ሰው መረጃዎችን በመሰብሰብ የክፍያ ሚዛን፣ የገንዘብ አቅርቦትና የዋጋ ትንበያዎችን እንዲሁም ለትንተናና የገንዘብ፣ የቁጠባና የምንዛሪ ፖሊሲዎችን ለመቀረጽና ለመወሰን የሚረዱትን ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጠቋሚ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የያዘ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠቃሚ የሆኑ ጥናቶችን በየጊዜው የማካሄድ፤

፲፬/ መንግሥትን በባንክ አገልግሎት፣ በገንዘብ ውክልናና በፋይናንስ አማካሪነት የማገልገል፤

፲፭/ የክፍያ፣ የማጣራትና የማወራረድ ሥርዓት የማቋቋም፣ ዘመናዊ የማድረግ፣የማካሄድ፣ የመከታተልና የመቆጣጠር፤

፲፮/ ኢትዮጵያ የተዋዋለቻቸውን ዓለም አቀፍ የገንዘብና የባንክ ስምምነቶች በማክበር የመሥራትና አገሪቱን በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንዲሁም በሌሎች በማዕከላዊ ባንኮች በተቋቋሙ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ዘንድ የመወከል፤

፲፯/ ልዩ የመታሰቢያ ሣንቲሞች የመቅረጽ፤

፲፰/ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የማቋቋምና የመምራት፤

፲፱/ ዓላማዎቹን ለማስፈጸም ማዕከላዊ ባንኮች በተለምዶ የሚኖራቸውን ሌሎች ሥልጣኖች መጠቀምና ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

## ፮. ካፒታልና የመጠባበቂያ ሂሣቦች

፩/ የብሔራዊ ባንክ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ይሆናል። የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ብር ፭፻ሚሊዮን (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ሊጨምር ይችላል።

፪/ ከተጣራ ትርፉ ውስጥ ፳ በመቶ (ሃያ በመቶ) የባንኩ የመጠባበቂያ ሂሣብ የተከፈለው የካፒታል መጠን ጋር እስኪስተካከል ድረስ በየበጀት ዓመቱ ወደዚሁ ሂሣብ ገቢ ይሆናል፤ ቀሪው ፹ በመቶ (ሰማንያ በመቶ) ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሂሣብ ገቢ ይሆናል።

፫/ ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከተከፈለው ካፒታል ጋር እኩል ሲሆን፣ የተጣራው ትርፍ በሙሉ በየበጀት ዓመቱ ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሂሣብ ገቢ ይሆናል።

፬/ የተጣራ የብሔራዊ ባንክ ኪሣራ ከጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ላይ ተቀናሽ ይሆናል።

12/ accept deposits of any kind from foreign sources;

13/ collect data from any person and prepare periodic economic studies, on the balance of payments, money supply, price forecasts and other relevant statistical indicators for analysis and for the formulation and determination of monetary, saving and exchange policies as are useful to Ethiopian economy;

14/ act as banker, fiscal agent and financial advisor to the Government;

15/ take such steps to establish, modernize, conduct, monitor, regulate and supervise payment, clearing and settlement systems;

16/ act in compliance with international monetary and banking agreements of Ethiopia and represent Ethiopia in the International Monetary Fund and other international financial organizations formed by central banks;

17/ coin special commemorative coins;

18/ establish and manage deposit insurance fund;

19/ exercise such other powers and functions to execute its purposes as central banks customarily perform.

## 6. Capital and Reserve

1/ The capital of the National Bank shall be totally owned by the Government. The paid up capital of the National Bank is Birr500,000,000 (five hundred million Birr) and may be increased as might be found necessary by regulation to be issued by the Council of Ministers.

2/ 20% (twenty percent) of the net profit shall be paid each financial year into the General Reserve Fund until such fund equals the paid up capital of the National Bank. The remaining 80% (eighty percent) shall be credited to the account of the Ministry of Finance and Economic Development.

3/ Where the General Reserve Fund equals the paid up capital of the Bank, the total amount of the net profit shall be credited each financial year to the account of the Ministry of Finance and Economic Development.

4/ Net losses of the National Bank shall be debited to the General Reserve Fund.

፭/ ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም ጊዜ በደረሰበት የተጣራ ኪሣራ የተነሣ ጠቅላላው የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከካፒታሉ ያነሰ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከባንኩ ካፒታል ጋር እንደገና እስኪስተካከል ድረስ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፮/ መንግሥት የብሔራዊ ባንክ ካፒታል በማናቸውም ጊዜ ሳይቀነስ እንደተጠበቀ መቆየቱን ያረጋግጣል፡፡

## ፯. የሂሣብ ዓመትና የሂሣብ መግለጫዎች

፩/ የብሔራዊ ባንክ የሂሣብ ዓመት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል፡፡

፪/ የብሔራዊ ባንክ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የሂሣብ ሚዛንና ከሂሣቦቹ ጋር የተያያዙ ማስታወሻዎች የሚሠሩት በዓለም አቀፍ የሂሣብ አያያዝ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

፫/ የብሔራዊ ባንክ የሂሣብ ዓመት ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውሰጥ ባንኩ ኦዲት ያልተደረገ የሂሣብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና የኪሣራውን መግለጫ አዘጋጅቶ ለመንግሥት ያቀርባል፡፡

## ፰. የውጭ ኦዲት

፩/ የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ በየዓመቱ የውጪ ኦዲተር ይሾማል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የባንኩ ቦርድ ኦዲት ኮሚቴ መርምሮ እንዲያፀድቀው መቅረብ አለበት፡፡ እያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በኦዲት ኮሚቴ የፀደቀው የኦዲት ሪፖርት ለመንግሥት መላክ ይኖርበታል፡፡

፪/ በኦዲተር በሚገባ የተመረመረና የተፈረመ የሂሣብ ሚዛንና የዓመቱን ትርፍና ኪሣራ የሚያሳይ መገለጫ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ውሰጥ ይታተማሉ፡፡

## ፱. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን፣ ተግባር እና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት የብሔራዊ ባንክ ሥልጣኖች፣ ኃላፊነቶች እና ተግባሮች ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተሰጥተዋል፡፡

5/ If at any time, as a result of net losses sustained by the National Bank, the General Reserve Fund is less than the paid up capital, the provisions of sub-article (2) of this Article shall be applied until the General Reserve Fund is again equal to the paid up capital.

6/ The Government shall ensure that the paid up capital of the National Bank remain intact at all times.

## 7. Financial Year and Financial Statements

1/ The financial year of the National Bank shall begin on July 1 and end on June 30 of the next year.

2/ The profit and loss account, balance sheet and notes to the accounts shall be prepared by the National Bank in accordance with international financial reporting standards.

3/ The National Bank shall, within three months from the end of each financial year, prepare and submit to the Government unedited balance sheet as well as profit and loss account.

## 8. External Audit

1/ The Board of Directors of the Bank shall appoint an external auditor annually. The audit report shall be completed and issued to the National Bank's Board of Directors' Audit Committee for review and approval, and subsequently submitted to the Government, within six months from the end of each financial year.

2/ A duly audited and signed by Auditor concerning balance sheet and annual profit and loss statement shall be published in the annual report to be issued by the National Bank.

## 9. Powers, Duties and Meeting Procedure of the Board of Directors

1/ The powers, responsibilities and functions of the National Bank provided for in this Proclamation shall be vested in the Board of Directors.

፪/ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አራቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከተገኙት አባላት አንዱ የባንኩ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ የቦርዱ ስብሰባዎች በሊቀመንበሩ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በወከለው የቦርድ አባል ይጠራል፡፡

፬/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ሊቀመንበሩ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በእርሱ የተወከለ ሰው ወይም ገዥው ወይም ከቦርዱ አባላት ሦስቱ ሲጠይቁ ስብሰባው በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡

፭/ የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

፮/ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈለው አበል መጠን በመንግሥት ይወሰናል፡፡

፯/ ማናቸውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባሎች አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤ ቦርዱ በድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፰/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ቦርዱ በሚወስነው አኳኋንና በትክክል ይመዘገባል፡፡ ቦርዱ በይፋ እንዲታወቅ ካልፈቀደ በቀር ማናቸውም ቃለ ጉባኤ በሚስጥር ይጠበቃል፡፡

፱/ የዳይሬክተሮች ቦርድ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣኑን ለገዥው በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፲፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ ሦስት የቦርድ አባላትን ያካተተ የኦዲት ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡ ኮሚቴው የውስጥና የውጭ ኦዲተሮችን ግኝትና የመፍትሄ ሃሣብ ተቀብሎ ይመረምራል፣ ለአፈጻጸሙም አስፈላጊውን መመሪያ ይሠጣል፡፡

## ፲. <u>የብሔራዊ ባንክ ገዥ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ የብሔራዊ ባንክ ገዥ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በዚህ አዋጅና በቦርዱ ውሣኔዎች መሠረት የባንኩን አስተዳደርና ሥራ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

2/ The presence of four members of the Board of Directors shall constitute a quorum; provided, however, that one of them shall be the Governor or Vice Governor.

3/ Meetings of the Board shall be called by the Chairperson or, in his absence, by a member of the Board delegated by him.

4/ Meetings of the Board of Directors shall be held at least once every three months; provided, however, that the Chairperson or, in his absence, the person delegated by him, may call a meeting at any time or when the Governor or three board members so request.

5/ The Board of Directors shall have its own secretary.

6/ The Government shall fix the amount of allowance payable to the members of the Board of Directors.

7/ All decisions of the Board of Directors shall be made by a simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

8/ Minutes of meetings of the Board of Directors shall be recorded accurately and in such form as the Board of Directors may determine. Unless the Board of Directors decides otherwise, minutes of the Board of Directors shall be confidential.

9/ The Board of Directors may adopt its own rules of procedure.

10/ The Board of Directors may, where it deems necessary, delegate its powers to the Governor.

11/ The Board of Directors shall have an Audit Committee composed of at least three board members. The Audit Committee shall receive and examine the findings and recommendations of the internal and external auditors and also give the necessary direction for the implementation.

## 10. <u>Powers and Duties of the Governor of the National Bank</u>

1/ The Governor of the National Bank shall be the chief executive officer of the Bank and, as such, shall direct and supervise the administration and operations of the Bank in accordance with this Proclamation and the decisions of the Board.

፪/ ገዥው የብሔራዊ ባንክን ዕቅድና አመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፫/ ገዥው የብሔራዊ ባንክ ዋና ተጠሪ በመሆን ባንኩ፣

ሀ) ከሌሎች ሰዎች፣ ከመንግሥት፣ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ብሔራዊ ባንክ አባል ከሆነባቸው የገንዘብ ድርጅቶች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ባንኩን ይወክላል፤

ለ) የሚያደርጋቸውን ውሎች፣ የሚያሳትማቸውን የገንዘብ ኖቶችና የዋስትና ሰነዶች፣ ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ የሂሣብ ሚዛን ሰነዶች፣ የትርፍና የኪሣራ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤ ዎችና ሌሎች የባንኩን ሰነዶች ብቻውን ወይም ከተፈቀደላቸው ሌሎች የባንኩ ሹማምንት ጋር በአንድነት ይፈርማል፣ እና

ሐ) በሚከስበት ወይም በሚከሰስበት ማናቸውም ጉዳይ ራሱ ወይም በነገረፈጅ አማካይነት የባንኩ ወኪል ይሆናል፡፡

፬/ ገዥው ለብሔራዊ ባንክ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ተግባሩንና ሥልጣኑን በከፊል ለምክትል ገዥውና ለሌሎች የባንኩ ሹማምንት በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፭/ ገዥው በማናቸውም ተግባሩ በአንቀጽ ፬ ላይ በተመለከቱት የብሔራዊ ባንክ ዓላማዎች ይመራል፡፡

## ፲፩. <u>የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ ሥልጣንና ተግባር</u>

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ የባንኩን ገዥ ይረዳል፤ ገዥው በሌለ ጊዜ ለገዥው የተሰጡትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ብሔራዊ ባንክ ከመንግሥት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

## ፲፪. <u>የመንግሥት የገንዘብ አስተዳደር ተወካይና ባንክ መሆን</u>

ብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት የመንግሥት ወኪልና ባንክ ሆኖ ይሠራል፤ በዚህም መሠረት በመንግሥት ስም እና ሂሣብ ለመንግሥት የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፤

2/ The Governor shall prepare the plans and annual budgets of the National Bank and, upon approval by the Board of Directors, implement the same.

3/ The Governor shall be the principal representative of the National Bank, and in this capacity shall:

a) represent the National Bank in its all relations with other persons, the Government, the International Monetary Fund and other relevant financial institutions in which the National Bank is a member;

b) sign individually or jointly with other authorized officers of the National Bank contracts concluded by the National Bank, currency notes or securities issued by the National Bank, annual reports, balance sheets, profit and loss statements, correspondence and other documents of the National Bank; and

c) represent the National Bank, either personally or through counsel, in any legal proceeding to which the National Bank is a party.

4/ The Governor may delegate part of his powers and duties to the Vice Governor and other officers of the National Bank, as may be required for the efficiency of the National Bank.

5/ The Governor shall, in all his actions, be guided by the purposes of the National Bank as set out in Article 4 of this Proclamation.

## 11. <u>Powers and Duties of the Vice Governor of the National Bank</u>

The Vice Governor of the National Bank shall assist the Governor and in the absence of the Governor shall discharge all the functions conferred on the Governor.

## <u>PART THREE</u>

## RELATIONS OF THE NATIONAL BANK <u>WITH THE GOVERNMENT</u>

## 12. <u>Fiscal Agent and Banker for the Government</u>

The National Bank shall act as a fiscal agent and banker for the Government and, in that capacity, it shall, in the name and for the account of the Government, engage in the following transactions:

፩/ ተቀማጭ ገንዘብ ይቀበላል፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቀማጭ ገንዘቦችን ይሰበስባል፣ በአደራ ያስቀምጣል፣ ክፍያም ይፈጽማል ወይም ያስተላልፋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ሌሎች ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ስም እነዚህን ተግባራት እንዲያከናውኑ ሊወክል ይችላል፤ በገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሲጠየቅ በዚህ አኳኋን የተያዙ ሂሣቦችን በሚመለከት መረጃዎችን ያቀርባል፤

፪/ ቼኮች፣ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ ሰነዶችና የዋስትና ሰነዶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል ወይም በአደራ ተረክቦ ያስቀምጣል፤

፫/ እንደ ወርቅና ብር ያሉትን የከበሩ ማዕድናትና የውጭ አገር ገንዘብ ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል ወይም በአደራ ተረክቦ ያስቀምጣል፤

፬/ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት በተለይ የተዘረዘሩ የመንግሥት ሂሣቦችን ያስተዳድራል፤

፭/ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን ሲሰጠው የመንግሥት ዕዳን ያስተዳድራል፤ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነዶችንና ቦንዶችን እንዲሁም ሌሎች የዋስትና ሰነዶችን ይሸጣል፣ ያስተዳድራል፤

፮/ ለመንግሥት ብድር ይሰጣል፤

፯/ በመንግሥት የወጡ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተላለፉ የግምጃ ቤት ሰነዶችና ቦንዶች ይገዛል፣ ይሸጣል::

## ፲፫. ብ ድ ር

፩/ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት የሚሰጠው የብድር መጠን ከባንኩ ጋር በሚደረግ ምክክር የሚወሰን ሆኖ የዋጋና የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ መረጋጋትን ከማስፈን ዓላማ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት::

፪/ ባንኩ ለመንግሥት፣ ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም ሰው በቀጥታ ብድር አይሰጥም::

## ክፍል አራት

## ብሔራዊ ባንክ ከባንኮች፣ ከመድን ሰጭ ድርጅቶችና ከሌሎችየገንዘብ ተቋማት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

## ፲፬. ፈቃድ ስለመስጠትና መቆጣጠር

ብሔራዊ ባንክ ለባንኮች፣ ለመድን ሰጪ ኩባንያዎችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል::

1/ accept deposits, collect or take custody of funds deposited by the Government in Ethiopia or abroad, and remit or effect payments and, where necessary, assign banks to carry out these functions in its name and for its account; furnish information regarding such accounts as and when requested by the Ministry of Finance and Economic Development;

2/ purchase, sell, transfer or take custody of cheques, bills of exchange, promissory notes and securities;

3/ purchase, sell, transfer or take custody of precious metals such as gold and silver, and foreign exchange;

4/ administer expressly specified Government accounts in accordance the arrangements to be made with the Ministry of Finance and Economic Development;

5/ upon authorization by the Ministry of Finance and Economic Development, manage public debt transactions; manage and sell treasury bills and bond and other securities of the Government;

6/ make advances to the Government;

7/ buy and sell unconditional negotiable treasury bills and government bonds issued by the Government.

## 13. Credits and Advances

1/ The amount of advances and credit to be extended by the National Bank to the Government for each fiscal year shall be determined in consultation with the Bank and shall be consistent with the maintenance of price and exchange rate stability.

2/ The National Bank shall not extend direct credit to any person other than the Government, banks and other financial institutions.

## PART FOUR

## RELATIONS OF THE NATIONAL BANK WITH BANKS, INSURANCE COMPANIES AND OTHER FINANCIAL INSTITUTIONS

## 14. Licensing and Regulation

The National Bank shall license and regulate banks, insurance companies and other financial institutions in accordance with the relevant laws of Ethiopia.

## ፲፭. የብድር አሰጣጥና አስተዳደር

፩/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ) ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሚዛናዊ ዕድገት ተስማሚ የሆነ የተረጋጋ የዋጋና የምንዛሪ ምጣኔ ለማስፈን፣

(፩) ከባንኮችና ከሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ጋር ስላለው የብድር ግንኙነት፣ እና

(፪) በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ስለሚሰጡ የብድር አገልግሎቶች፣

መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

ለ) እንደነገሩ ሁኔታ በአግባቡ የተፈረሙና በባለቤቱ በጀርባ በመፈረም የተረጋገጡ የሐዋላ ሰነዶች፣ የተስፋ ሰነዶች፣ አክሴፕታንሶችና ሌሎች የገንዘብ መክፈያ ሰነዶች በቅናሽ ወይም ድጋሚ ቅናሽ በማድረግ የሚገዛበት ወይም የሚሸጥበት፣ ከባንኮችና ከሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ጋር የሚሠራበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፤

ሐ) ቅናሽ ወይም ድጋሚ ቅናሽ በማድረግ በሚቀበላቸው ሕጋዊ ሰነዶች ላይ የሚከፈለውን የወለድ መጠን ይወስናል፤

መ) በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ግዴታዎችና ሁኔታዎች መሠረት ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ብድር ሊሰጥ ይችላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሀገሪቱ ውስጥ በሰፊው በሚሠራጩ ጋዜጦች ታትመው እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል።

## ፲፮. ሌሎች ተግባሮችና አገልግሎቶች

፩/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ) ባንኮች፣ መድን ሰጪ ኩባንያዎችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት በተቀበሉት ተቀማጭ ገንዘብ ላይ ወይም በሌላ መለኪያ ላይ ተመሥርቶ በሚሠላ መጠን በጥሬ ገንዘብ፣ በሌላ ገንዘብ አከል ንብረቶችና በመንግሥት የዋስትና ሰነድ የሚይዙትን የሀብት መጠን ሊወስንና ይሄው ሀብት በባንኩ እንዲቀመጥ በየጊዜው ሊያዝ ይችላል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ከተገለጸው በተጨማሪ ከባንኮችና ከሌሎች የገንዘብ ተቋማት በአደራ ገንዘብ ተቀብሎ ሊያስቀምጥ እንዲሁም በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ስም ወይም ስለእነርሱ ሆኖ ገንዘብ ሊቀበል ይችላል፤

## 15. Credit Extension and Management

1/ The National Bank:

a) for the purpose of maintaining price and exchange rate stability that is conducive to the balanced growth of the economy of Ethiopia, may issue directive governing:

(1) its own credit transactions with banks and other financial institutions; and

(2) credit transaction of banks and other financial institute-ions**;**

b) may engage with banks and other financial institutions in transactions involving the discount, rediscount, purchase or sale, as the case may be, of duly signed and endorsed bills of exchange, promissory notes, acceptances and other credit instruments on the basis of directives issued by it for this purpose;

c) shall determine the rate of interest of legal instruments accepted by it up on discount or rediscount;

d) may make loans or advances to banks and other financial institutions on the basis of obligations and conditions determined by its directive.

2/ The measures taken by the National Bank pursuant to sub-article (1) of this Article may, where necessary, be published in newspapers of wider circulation.

## 16. Other Functions and Services

1/ The National Bank may:

a) timely determine, on the basis of accessing the received deposit or any other scale, the amount of assets to be held by banks, insurance companies and other financial institutions in the form of cash, other liquid assets and government securities; and also timely order the deposit of the same asset with it;

b) in addition to what is stated under Sub-Article (1) (a) of this Article, accept money on deposit from, and collect money for and on account of, banks and other financial institutions;

ሐ) ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት የክፍያና የክሊሪንግ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፤

መ) የባንኮችንና የሌሎችን የገንዘብ ተቋማት ሂሣብ ሊይዝና ወኪላቸው ወይም ተጠሪያቸው ሆኖ ሊሠራ ይችላል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል፤ የክፍያውን መጠን ለባንኮቹ እና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት በቅድሚያ ያሳውቃል::

## ክፍል አምስት

## የገንዘብ መደብ ልክና ሕጋዊ ገንዘብ

### ፲፯. የገንዘብ መደብ

፩/ የኢትዮጵያ የገንዘብ መደብ ብር ሲሆን የሀገሪቱ ሕጋዊ ገንዘብ ይሆናል:: የብር ኦፊሴላዊ አጭር ስያሜ "ብር" የሚል ይሆናል:: "ኢትብ" የሚለው የብር ዓለም አቀፋዊ አጭር ስያሜ ይሆናል::

፪/ የገንዘብ መደቡ "ሳንቲሞች" ተብለው በሚጠሩና እኩል በሆኑ አንድ መቶ ክፍልፋዮች ይከፈላል:: የሣንቲም አጭር ስያሜ "ሳ" ይሆናል::

፫/ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተደረገ ስምምነት እስካልሆነ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉ ማናቸውም የገንዘብ ስምምነቶችና ውሎች በብር እንደተፈጸሙ ይቆጠራል::

፬/ ብሔራዊ ባንክ በሌላ አኳኋን ካልፈቀደ ወይም ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም የአገሪቷ ሕጎች ላይ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም የገንዘብ ግንኙነቶች ሁሉ የሚመዘገቡትና የሚከፈሉት በብር ይሆናል::

### ፲፰. ሕጋዊ ገንዘብ

፩/ በገንዘብ ኖቶች ላይ የሚጻፈው ጽሑፍ፣ የኖቶቹ ስፋት፣ ቅርጽና መደባቸው እንዲሁም ሌሎች ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል::

፪/ የቅንስናሽ ገንዘቦች ክብደት፣ ጥራት፣ ጽሑፍ፣ ስፋት፣ ቅርጽ፣ መደብና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል:: በተመሣሣይ የመታሰቢያ ሣንቲሞች ሕጋዊ ተቀባይነት፣ ብዛት፣ ክብደት፣ ጥራት፣ ጽሑፍ፣ ስፋት፣ ቅርጽና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል::

c) provide payments and clearing services to banks and other financial institutions;

d) keep balances and act as agent or correspondent of banks and other financial institutions.

2/ The National Bank may charge fees for the services referred to Sub-Article (1) of this Article. Such fees shall be communicated in advance to the banks and other financial institutions.

## PART FIVE

## THE MONETARY UNIT AND LEGAL TENDER

### 17. Monetary Unit

1/ The monetary unit of Ethiopia shall be Birr and it shall be the legal tender of the country. The official abbreviation of the Birr shall be “Br”, and “ETB” shall be the international currency code.

2/ The Monetary unit shall be divided into one hundred equal parts, named “cents”, the official abbreviation of which shall be “Ct”.

3/ All monetary transactions taking place in Ethiopia shall be presumed to be expressed in Birr unless validly agreed upon otherwise by the permission of the National Bank.

4/ All monetary transactions shall be recorded and settled in Birr unless otherwise authorized by the National Bank or provided for in any international agreement to which Ethiopia is a party or in any domestic law.

### 18. Legal Tender

1/ The inscription, dimension, design, denomination and other characteristics of legal tender notes shall be determined by the National Bank.

2/ The weight, fineness, inscription, dimension, design, denomination and other characteristics of coins shall be determined by the National Bank. Similarly, values of commemorative coins at which they shall be accepted as legal tender, their numbers to be minted, weight, fineness, inscription, dimension, design and other characteristics thereof shall be determined by the National Bank.

፫/ ኢትዮጵያ ውስጥ በዝውውር ላይ ያሉ ሕጋዊ የብር ኖቶች ሁሉ ማናቸውንም የመንግሥትም ሆነ የግል ዕዳ ያለገደብ ለመክፈል ሕጋዊ ገንዘብ ናቸው፡፡

፬/ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ሆነው በዝውውር ላይ ያሉ ቅንስናሽ ገንዘቦች ማናቸውንም የመንግሥትም ሆነ የግል ዕዳ ለመክፈል ሕጋዊ ገንዘብ ናቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖቹ በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር ዕዳ ለመክፈል የሚውለው የቅንስናሽ ገንዘብ መጠን ከአሥር ብር አይበልጥም፡፡ ሆኖም ብሔራዊ ባንክም ሆነ ሌሎች ባንኮች በማንኛውም አምጪ ጥያቄ ቅንስናሽ ገንዘቦቹን ወደ ኖቶች መቀየር አለባቸው፡፡

፭/ ብሔራዊ ባንክ በማናቸውም ጊዜ የብር ኖቶችን ወይም ሣንቲሞችን የአስመስሎ ሥራት መከላከያ ግልጽና ስውር ምልክቶች የቀየረ እንደሆነ፣ ወይም በሥራ ላይ የነበረ ኖት ወይም የተለየ መደብ ያለው ኖት ወይም ሣንቲም ከተወሰነ ቀን በኋላ ሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብነቱ መቅረቱን፣ መመሪያ በማውጣት ሊያሳውቅ ይችላል፤ የተደረገውን ለውጥ በሰፊው በሚሰራጩ ጋዜጦችና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ይገልጻል፤ የሚለወጡትን ኖቶችና ሣንቲሞች የያዙ ሁሉ በአዲሶቹ ኖቶችና ሣንቲሞች የሚለውጡበት በቂ ጊዜ ይሰጣል፡፡

፮/ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ማንኛውም ሰው በባንኩ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው በላይ የኢትዮጵያን ገንዘብ ይዞ ወደ ሃገር ውስጥ ለመግባት ወይም ለመውጣት አይችልም፡፡

## ክፍል ስድስት

## ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሣብና የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር

### ፲፱. ዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሣብ ስለመያዝ

፩/ ብሔራዊ ባንክ የውጭ አገር ገንዘብ፣ የግዴታ ሰነዶች፣ ወርቅ ወይም ሌሎች ዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ንብረቶችን ያካተተ ሂሣብ ይኖረዋል፡፡

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚይዘው ዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሣብ በማናቸውም ጊዜ፣

ሀ) በአስቸኳይና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከውጭ ሃገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ክፍያን፣

ለ) የውጭ አገር ዕዳ ክፍያ ግዴታዎችን፣ እና

3/ Birr notes lawfully in circulation within Ethiopia shall be unlimited legal tender in the settlement of all public or private debts.

4/ Coins lawfully in circulation within Ethiopia shall be legal tender in the settlement of all public and private debts. Unless the parties agreed otherwise, the amount of coins used for settlement of such debts shall not exceed ten Birr; provided, however, that the National Bank and other banks shall, at the request of any holder, change into notes the holder's coins.

5/ Whenever the security and features of a particular issue or denomination of notes or coins are changed or a particular issue or denomination of notes or coins cease to be legal tender as of a certain date, the National Bank shall declare such change or withdrawal by directives. The National Bank shall also announce such declaration through newspapers of wider circulation and other communication media. The National Bank shall give to holders of such notes and coins reasonable time within which to exchange such notes and coins for new ones.

6/ No person entering into, or departing from, Ethiopia shall carry with him an amount of Ethiopian currency in excess of an amount fixed or permitted by the National Bank.

## PART SIX

## INTERNATIONAL RESERVE FUND AND FOREIGN EXCHANGE ADMINSTRATION

### 19. Maintaining International Reserve Fund

1/ The National Bank shall maintain among its assets an international reserve fund consisting of foreign currencies, foreign securities, gold or other international reserve assets.

2/ The National Bank shall endeavor to maintain, at all times, sufficient international reserve fund as provided for in sub-article (1) of this Article, to cover:

a) payments for immediate and short term imports of commodities and services into Ethiopia;

b) foreign debt payment commitments; and

ሐ) የመሠረታዊ አገልግሎቶች ክፍያን፣

በበቂ ሁኔታ ለመሸፈን የሚያስችል እንዲሆን ጥረት ያደርጋል::

፫/ የዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ገንዘብ ከሚያስፈልገው መጠን ያነሰ እንደሆነ ወይም ሊያንስ እንደሚችል ገዥው ካመነበት ወይም የመጠባበቂያ ገንዘቡ በቂነት የመቀነስ አዝማሚያ እያሣየ መሆኑን ሲገነዘብ የመጠባበቂያ ገንዘቡን ይዞታ፣ ለሁኔታው መንስኤ የሆኑትን ወይም ሊሆኑ የሚችሉትን ምክንያቶች እና ሁኔታውን ለማሻሻል አስፈላጊ የመሰለውን የመፍትሄ እርምጃ የያዘ የውሳኔ ሃሳብ ለባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል:: ችግሩ እየተባባሰ መሄዱን ከተገነዘበ ገዥው የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዳይሰጥ ሊያግድ ይችላል::

፬/ ብሔራዊ ባንክ ለባንኩና ለሃገሪቱ ጠቃሚ ሆነው የሚታዩትን የሁለትዮሽና ሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብና የክፍያ እንዲሁም ተዛማጅ ስምምነቶች ሊዋዋል ይችላል::

## ፳. <u>የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ፈቃድ ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሔራዊ ባንክ የተለየ ፈቃድ ካላገኘ በቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሠማራት አይፈቀድለትም::

፪/ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ፣ ነዋሪ ያልሆኑና ለጉብኝት የመጡ ሰዎች ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው የውጭ ምንዛሪ የሚይዝበትን ወይም በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚፈጽምበትን ወይም የክፍያ ማዘዣዎችን የሚይዝበትንና የሚጠቀምበትን ሁኔታዎችና ገደቦች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል::

፫/ ማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ የሚተላለፍ የውጭ ምንዛሪ፣ በወጪ ወይም በገቢ ንግድ አማካይነት ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ወይም ሌሎች ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች በማናቸውም አኳኋን የኢትዮጵያን የጉምሩክ ድንበር አቋርጠው የሚወጡበት፣ እነዚህ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚመለሱበት፣ ወይም ከላይ የተመለከቱት ወደ ውጭ የተላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ወይም ከውጭ የተመለሱ ዕቃዎች በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የሚያስከትሉት ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጤት የሚመለከቱ ግዴታዎችና ሁኔታዎች ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

፬/ ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን ካላረጋገጠ በስተቀር የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማናቸውም ዋጋ ያለው ዕቃ ወይም የውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ወይም እንዲገባ አይፈቀድም::

፭/ ባንኮች፣ የመድን ሰጪ ኩባንያዎችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት በውጭ ምንዛሪ የሚያደርጉትን ልውውጥ ወይም ግብይት ብሔራዊ ባንክ በቦታው ተገኝቶ በመመርመር ወይም በሚቀርቡለት መረጃ ዎች መሠረት በመከታተል መቆጣጠር ይችላል::

c) payments for basic services.

3/ If the international reserve has declined or, in the opinion of the Governor, appears to be in danger of declining or is at such a level that the Governor considers its adequacy in jeopardy, the Governor shall submit a report to the Board of Directors of the National Bank on the international reserve fund position and the causes that have led to, or may lead to, such a decline, together with recommendations concerning the measures the Governor considers necessary to forestall or otherwise remedy the situation. When the situation persists, the Governor may decline issuance of further foreign exchange permit.

4/ The National Bank may enter into bilateral or other international monetary, payment and related agreements which it deems are in the interest of the Bank and the country.

## 20. <u>Regulation of Foreign Exchange</u>

1/ No person shall engage in any transaction of foreign exchange except with banks or authorized dealers or with the special permission of the National Bank.

2/ The conditions, limitations and circumstances under which residents of Ethiopia, and non-residents visiting Ethiopia, or any other person may possess and utilize foreign currency or instruments of payments in foreign exchange shall be determined by directive to be issued by the National Bank.

3/ The terms and conditions for transfer of foreign exchange to and from Ethiopia, and the export or import of valuable goods or the transfer of other valuable goods across the customs boundaries or frontiers of Ethiopia in any manner, the return of such goods and the settlement of any foreign exchange that results, or that will result, from such export or import or transfer shall be determined by directive to be issued by of the National Bank.

4/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall not allow import or export of valuable goods or foreign exchange unless conditions, circumstances and terms determined by the National Bank are fulfilled.

5/ The National Bank shall monitor foreign exchange transactions of banks, insurance companies and other financial institutions through on-site inspection and off-site surveillance.

፮/ ማንኛውም ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ ሥልጣን የተሰጠው መንዛሪ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና በብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተደነገጉት መፈጸም ወይም አለመፈጸማቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በእጁ የሚገኙትን ወይም የሚያዝባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች፣ የሂሣብ መዛግብትና ሌሎች ሰነዶች በብሔራዊ ባንክ ሲታዘዝ ለባንኩ ወይም ባንኩ ለመደበው ወኪል ማቅረብ አለበት፡፡

**፳፩. <u>በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ንብረቶች ስለሚደረግ ግብይት</u>**

፩/ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ሃገር ገንዘብ ኖቶች እና ቅንስናሽ ገንዘቦች እንዲሁም በዓለም አቀፍ ክፍያ ወይም ለገንዘብ ማስተላለፊያነት በተለምዶ የሚሠራባቸውን የገንዘብ ማዘዋወሪያና ሌሎች ሰነዶች፣ ሐዋላዎች የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለመግዛት፣ ለመሸጥና ለመያዝ ይችላል፡፡

፪/ ብሔራዊ ባንክ በውጭ ሃገር ማዕከላዊ ባንኮች፣ በራሱ ወኪሎች ወይም የውጭ ተጠሪ ባንኮች ዘንድ በውጭ ሃገር ገንዘብ ሂሣብ ሊኖረውና ይህንንም ገንዘብ እንደአስፈላጊነቱ በጊዜ ገደብ ተቀማጭ፣ በወርቅ፣ እንደልብ ሊተላለፉ በሚችሉ የውጭ ሃገር የዋስትና ሰነዶችና በሌሎች ኢንቨስትመንቶች ሊያውል ይችላል፡፡

፫/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት፣

ለ) ከመንግሥት፣ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተቋሞች፣

ሐ) ከውጭ ሃገር ማዕከላዊ ባንኮች፣ ከውጭ ሃገር ባንኮችና የገንዘብ ተቋሞች፣

መ) ከውጭ መንግሥታትና መሥሪያ ቤቶቻቸው፣ እና

ሠ) ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት፣

ጋር የውጭ ሃገር ገንዘብ ምንዛሪ ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡

፬/ ሌላ ተቃራኒ የሕግ ድንጋጌ ሳያግደው ብሔራዊ ባንክ በራሱ ውሳኔ ብቻ ወርቅና ብር የመሳሰሉ የከበሩ ማዕድናት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ለመግዛት፣ ለመሸጥ፣ ለማስቀመጥ ወይም በሌላ ሁኔታ ለመገበያየት ይችላል፡፡

፭/ ብሔራዊ ባንክ፣

ሀ) የመድን ሰጪ ኩባንያዎች፣ ሌሎች የገንዘብ ተቋማትና ሥልጣን የተሰጣቸው መንዛሪዎች በውጭ ምንዛሪ፣ በወርቅ ወይም በብር ግብይት እንዲሳተፉ ሥልጣን ሊሰጣቸው ይችላል፤

6/ Any bank, insurance company, authorized dealer or any other person shall, when directed by the National Bank, produce to it or its designated representative all information, books, records, accounts and other documents in its possession or control which may be required for the purpose of ascertaining whether or not the provisions of this Proclamation and directives issued by the National Bank are complied with.

**21. <u>Transactions in International Reserve Assets</u>**

1/ The National Bank may buy, sell and hold foreign currency notes and coins and such other documents and instruments using various media as are customarily employed in international payments or transfers of funds.

2/ The National Bank may keep balances, denominated in foreign currencies, with foreign central banks, its agents or correspondents abroad, and may invest, at its discretion, such balances in time deposits, gold, readily negotiable foreign securities and other investment instruments.

3/ The National Bank may engage in foreign exchange transactions with the following:

a) banks and other financial institutions in Ethiopia;

b) the Government, its agencies, and institutions;

c) foreign central banks, foreign banks and financial institutions;

d) foreign governments and agencies; and

e) international financial institutions.

4/ Notwithstanding any other contrary provisions of law, the National Bank may, at its sole discretion, import, export, buy, sell, hold or otherwise deal in precious metals such as gold and silver.

5/ The National Bank may:

a) appoint insurance companies, other financial institutions and authorized dealers to engage in transactions involving foreign exchange, gold or silver;

ለ) የውጭ ምንዛሪ፣ የወርቅና የብር ግብይትን አስመልክቶ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፤

ሐ) ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ እንዲሰጡ ሊወክላቸው ይችላል::

b) issue directives relating to transactions in foreign exchange, gold or silver;

c) delegate banks and other financial institutions to issue foreign exchange permits.

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### ፳፪. መረጃ ስለመሰብሰብና ስለመስጠት

፩/ ብሔራዊ ባንክ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስፈልገውን ማናቸውንም መረጃ ከባንኮች፣ ከመድን ሰጪዎች፣ ከአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከማንኛውም ሰው መጠየቅና መቀበል ይችላል::

፪/ መረጃው የሚሰጠው፣

ሀ) በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ለማስፈጸም ፣

ለ) የባንኮች፣ የመድን ሰጪዎችና የሌሎች የገንዘብ ተቋማት የፋይናንስ ጤናማነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሐ) መረጃውን ለመቀበል ሕጋዊ ሥልጣን ላላቸው፣

መ) ባንኩ ተጠሪ ለሆነለት አካል፣ ወይም

ሠ) በፍርድ ቤት የታዘዘ ፣

ካልሆነ በስተቀር ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የተቀበለውን መረጃ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ላለ ማንኛውም ሰው አሣልፎ አይሰጥም::

፫/ ማናቸውም ባንክ፣ መድን ሰጪ፣ ሌላ የፋይናንስ ተቋም ወይም በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ማናቸው ንም ተግባሮች የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት ያወቀውን ወይም የያዘውን ማንኛውንም ሰው ወይም ድርጅት የሚመለከት መረጃ፣

ሀ) ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሲጠይቅ፣

### 22. Collecting and Disclosure of Information

1/ The National Bank is empowered to collect any information from banks, insurers, micro-finance institutions and any other persons as it may deem appropriate to carry out its duties and responsibilities.

2/ The National Bank shall not disclose the information it collected using its authority under sub-article (1) of this Article to any person, whether within or outside Ethiopia unless the disclosure is:

a) for the purpose of fulfilling the requirements of this Proclamation;

b) in the interest of ensuring the financial soundness of banks, insurers and other financial institutions;

c) to recipients who are legally authorized to obtain such information;

d) to the body to which the National Bank is accountable; or

e) ordered by a court.

3/ No bank, insurer, other financial institution or any other person exercising any function provided under this Proclamation shall, whether within or outside Ethiopia, disclose any information relating to any person or business which comes into his possession or knowledge except:

a) when requested by the National Bank in accordance with Sub-Article (1) of this Article;

ለ) መረጃውን ለመቀበል ሕጋዊ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሲጠይቁ፣ ወይም

ሐ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚገኝ ለማንኛውም ሰው መስጠት አይችልም።

## ፳፫. ከግብርና ከቀረጥ ነጻ ስለመሆን

፩/ ብሔራዊ ባንክ ከገቢ ግብር እንዲሁም ከውጭ ሃገር በሚያስገባቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር ገንዘብ ኖቶችና ሣንቲሞች እንዲሁም የመንገደኞች ቼኮች ላይ ሊጣል ከሚችለው ተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ ከጉምሩክ ታክስ ወይም ቀረጥ ነጻ ይሆናል።

፪/ ብሔራዊ ባንክ ወርቅና ብር እንዲሁም የብር ኖቶችንና ቅንስናሽ ሣንቲሞች በውጭ ምንዛሪም ሆነ በሃገር ውስጥ ገንዘብ ወደ ሃገር ውስጥ ሲያስገባም ሆነ ሲያስወጣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን የመሙላት ግዴታ የለበትም።

## ፳፬. ስለሠራተኞች አስተዳደር

የብሔራዊ ባንክ ሠራተኞችና የሥራ አመራር አባላት አስተዳደር በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ይሆናል።

## ፳፭. ስለተቀማጭ መድን ፈንድ ተቋም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተቀማጭ መድን ፈንድ ስለሚቋቋምበትና ስለሚተዳደርበት ሁኔታ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ፳፮. ስለቅጣት

፩/ ማንኛውም ሰው፣

ሀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ፣

(፩) በውጭ ምንዛሪ ግብይት የተሳተፈ ወይም የውጭ ምንዛሪ ሲያገኝ ወይም ለማግኘት መብት እንዳለው ሲያውቅ ለባንክ ወይም ፈቃድ ለተሰጠው መንዛሪ ያላሳወቀ እንደሆነ፣

(፪) የውጭ ምንዛሪ የተቀበለ ወይም በውጭ ምንዛሪ ክፍያ የፈጸመ እንደሆነ፣

(፫) የውጭ ምንዛሪ የሚቀበልበትን ጊዜ ያዘገየ ወይም የመቀበል መብቱን የተወ እንደሆነ፣

b) when legally authorized persons request for such information; or

c) when ordered to do so by a court.

## 23. Exemption from Taxes

1/ The National Bank shall be exempted from the payment of income tax and from value added tax and customs duties and taxes in respect of local and foreign currency notes and coins it imports and traveler's checks.

2/ The National Bank shall be exempted from making customs declaration when importing or exporting gold and silver and local and foreign currency notes and coins.

## 24. Staff Regulations

The employees and management staff of the National Bank shall be administered in accordance with regulation to be issued by the Council of Ministers.

## 25. Deposit Insurance Fund

The Council of Ministers may issue regulation on the establishment and management of Deposit Insurance Fund.

## 26. Penalties

1/ Whosoever:

a) in violation of the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued pursuant to this Proclamation:

(1) engages in transactions of foreign exchange or fails to declare to a bank or authorized dealer when he acquires foreign exchange or the right to receive foreign exchange;

(2) receives or effects payments in foreign exchange;

(3) delays his receipt or extinguishes his right to receive foreign exchange;

(፬) በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያ ገንዘብ ይዞ ከኢትዮጵያ የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ወይም የገባ ወይም ለመግባት የሞከረ እንደሆነ፣ ወይም

(፭) በብሔራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የውጭ ምንዛሪ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፣

ለ) የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ወይም አተገባበራቸውን ለማዛባት በማሰብ ማናቸውንም ሰነድ ያጠፋ፣ የቀደደ፣ ይዘቱን የቀየረ፣ የደለዘ ወይም የደበቀ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረበ ወይም ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ እንደሆነ፣

ሐ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፪ የተደነገገውን በመተላለፍ ማናቸውንም መረጃ ለማይገባቸው ሰዎች የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ) ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በማናቸውም ሌላ መንገድ የተላለፈ ወይም አተገባበራቸውን ያሰናከለ እንደሆነ፣

ወንጀል የሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት በወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

ሀ) ወንጀሉ የተፈጸመው ሥልጣንን አለአግባብ በመጠቀም ወይም በመንግሥት ሥራ አጋጣሚ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትን ለማካበት ወይም በተደጋጋሚ ሲሆን ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ከ፲፭ ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራትና ከብር፶ሺ እስከ ብር፻ሺ የገንዘብ መቀጫ ይሆናል፤

ለ) የወንጀል ድርጊቱ ከገንዘብ፣ ከወርቅ፣ ከዋስትና ሰነድ፣ ከዕቃ ወይም ከማናቸውም ሌላ ንብረት ጋር የተያያዘ ሲሆን ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱና የእሥራት ቅጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር እስከ ንብረቱ ዋጋ ሦስት እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል፤

(4) leaves or attempts to leave or enters or attempts to enter Ethiopian territory carrying Ethiopian currency in excess of the amount fixed or authorized by the National Bank; or

(5) is found carrying foreign exchange in excess of the amount fixed or authorized by the National Bank;

b) with intent to evade the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued pursuant to this Proclamation or to distort their application destroy, tears apart, alters, deletes or hides a document or produces false evidence or makes false declaration;

c) discloses information in violation of Article 22 of this Proclamation; or

d) in any other manner violates or obstructs the implementation of this Proclamation or regulations or directives issued pursuant to this Proclamation;

shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be punishable in accordance with the provisions of the Criminal Code.

2/ Unless a higher penalty is applicable under the Criminal Code pursuant to sub-article (1) of this Article:

a) the punishment shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be rigorous imprisonment not exceeding 15 years and fine not less than Birr 50,000 and not exceeding Birr 100,000 where the accused misused the power of his official position or where he committed the offence with intent to improperly amass wealth or where the offence is committed repeatedly;

b) where the offence is connected with currency, gold, security, goods or any other property, the fine shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed and the punishment of imprisonment, not exceed three times the value of the property unless it is lower than that imposed under paragraph (a) of this sub-article;

ሐ) ወንጀሉ የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ሲሆን ወንጀሉ የተሠራበት ንብረት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብ ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) መሠረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር ድርጊቱ ከተፈጸመበት ወርቅ፣ ገንዘብ፣ የዋስትና ሰነድ፣ ዕቃ ወይም ሌላ ንብረት ዋጋ እስከ ስድስት እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል፤

፫/ የገቢ ወይም የወጪ ንግድ ዕቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሣንሶ ያቀረበ ማንኛውም ሰው፣ ወንጀል የተሠራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ሀ) ከተመለከተው የገንዘብ ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር ድርጊቱ ከተፈጸመበት ንብረት ዋጋ እስከ ሦስት እጥፍ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣትና ከ፲፭ እስከ ፳፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

፬/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ማንኛውም የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ከሆነ ድርጅቱን ይመራ የነበረው ዳይሬክተር ወይም ባለሥልጣን ድርጅቱ ድርጊቱን መፈጸሙን እንደማያውቅና በተገቢው ጥረትም ሊያውቀው እንደማይችል በበቂ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር ከድርጅቱ ጋር ተጠያቂ በመሆን ከሰባት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከብር ፶ሺ እስከ ብር ፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል::

፭/ የወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው የሕግ ሰውነት ባለው ድርጅት ሠራተኛ ወይም ወኪል ከሆነና ሠራተኛው ወይም ወኪሉ የድርጊቱን መፈጸም የማያውቅና በተገቢው ጥረትም ሊያውቀው እንደማይችል በበቂ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ይቀጣል::

**፳፯. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

፪/ ብሔራዊ ባንክ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስ ፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል::

c) where the offence is committed by a body corporate, the fine may, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be raised to six times the value of gold, currency, security, goods or any other property with which the offence is committed unless it is lower than that imposed under paragraph (a) of this sub-article.

3/ Whosoever commits over or under invoicing of imported or exported goods shall, without prejudice to the confiscation of the property with which the offence is committed, be punishable with fine up to three times the value of the property unless it is lower than the fine specified under sub-article (2)(a) of this Article, and with rigorous imprisonment from 15 to 25 years.

4/ Where any offence under this Article is committed by a body corporate, the director or any other official who was, at the time of the commission of the offence, responsible for the management of the body corporate shall be jointly liable and shall be punishable with rigorous imprisonment from seven to ten years and with fine from Birr 50,000 to Birr 100,000, unless he can prove sufficiently to of the court that he had no knowledge and could not, by the exercise of reasonable diligence, have had knowledge of the commission of the offence.

5/ Where the offence is committed by an employee or an agent of a body corporate, such employee or agent shall be punishable in accordance with sub-article (4) of this Article, unless he can prove sufficiently to the court that he had no knowledge and could not, by the exercise of reasonable diligence, have had knowledge of the commission of the offence.

**27. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The National Bank may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

**፳፰. <u>ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር ፹፫/፲፱፻፹፮ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**28. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ The Monetary and Banking Proclamation No. 83/1994 is hereby repealed.

2/ No law, regulation or directive, inconsistent with the provisions of this Proclamation, shall have force with respect to matters provided for in this Proclamation.

**29.** Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of August, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**